# “ከመቶ ዓመት የቤት ሥራ” ያፈተለከው የኦነግ አቋም

በአሉላ (alulla2@yahoo.com) ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የሚለውን የድርጅቱን ፕሮግራም በመሠረዝ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር ከተቀሩት የኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ወያኔን እንደሚታገል ባለፈው ታህሳስ 22, 2004 ዓ.ም. (January 01, 2012) ባወጣው ድርጅታዊ መግለጫ አሳውቋል። የኦሮሞና የሁሉም ኢትዮጵያ ልጆች የትግል ውጤት። በትንሹ የ40 ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረው ኦነግ የኦሮሞ ብሔር መብት በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር መፈታት እንዳለበትና ለዚህም የፕሮግራም ለውጥ ማድረጉን ማሳወቁ እሰየው የሚያሰኝ አንድ እርምጃ ነው። ኦነግ ያወጣው የአቋም ለውጥ በሌላኛው የኦነግ አካል የተወገዘ መሆኑን በማጥላላት ሌላ መግለጫ ቢሰጥበትም የኦሮሞ ልጆች የዴሞክራሲና መብት ትግላቸውን በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ለማድረግ በአንጋፋ ድርጅታቸው ኦነግ ስም ሲያወጡ በቀጣይነት የሚጠየቁና ምላሽ የሚፈልጉ ጉዳዮች ቢኖሩም ይህ የኦነግ ክፍል ሊደገፍና ሊበረታታ ይገባዋል። ኦነግ የመገንጠል ጥያቄውን አንስቶ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ለመታገል ለመጀመሪያ ጊዜ ኦፊሴላዊ መግለጫ ሲሰጥ፣ ሲጠየቅ የነበረው ምላሽ ሲያገኝ፣ መደገፍና ማበረታታት ብልህነት ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ መብት የትግል ታሪክ የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄ ዋነኛው እንደነበር ለጥያቄ የሚቀርብ አልነበረም። በትንሹ ከዛሬ 40 ዓመት በፊት “የብሔሮች ጥያቄ ማንሳት አለመግባባትና ብጥብጥን ይፈጥራል፤ ሕዝብን ይለያይና የሀገሪቱ ሁኔታ ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል፤ ታምቆ የኖረው በጎሳዎች መካከል ያለው ቂምና ጥላቻ ፈንድቶ ታላቅ ፍጅት ይፈጥራል፤ ሀገሪቱም ተከፋፍላ፣ በብዙ ደምና መስዋዕትነት የተገነባው የኢትዮጵያ አንድነት ይፈርሳል…ወዘተ.” የሚሉ አባባሎች የተደመጡ ቢሆንም ነባራዊውን ሁኔታና የነበረውን የብሔር ጭቆና ተቀብሎ ችግሩን ለመፍታት መጣር በተገባ ነበር። በየጊዜው የተፈራረቁት አገዛዞች: ዓይው የኋላ ቀር ፊውዳላዊ የብዝበዛ ሰንሰለት እንዳይበጠስባቸው፣ ደርግ ፋሽስታዊ አፋኝ ሥርዓቱን ዕድሜ ለማራዘም፣ በሀገር አንድነት ስም ይበልጥ ግፉንና መከራውን አባብሰውት፣ ሀገር ከአንዱ አጥፊ ወደሌላው እየተንከባለለች እንደውም መበታተንን አጀንዳው አደረገው ወያኔ ላይ ልትወድቅ በቅታለች።

ደርግ በሀገር አንድነት ስም በኤርትራ ወገኖቻችን ላይ ያዘነበው የ17 ዓመት ጥይትና ቦንብ ለችግሩ መፍትሄ አላስገኘም። የኤርትራ አዛውንት፣ ወጣቶችና ሕጻናት ላይ የዘነበው ግፍ የመገነጣጠል ዓላማ ይዘው የተነሱትን ይጠናከሩ ዘንድ አመቻቸላቸው እንጂ የኢትዮጵያን አንድነት ሊያስጠብቅ አልቻለም። ቦንብና ጥይት ብሎም ጦርነትን የችግሮች መፍቻ አድርጎ መውሰድ፣ ይበልጥ ምሬትን፣ ይበልጥ ሰቆቃን፣ ይበልጥ መራራቅን ይፈጥራልና። ለኤርትራ መገንጠል የወያኔ አገዛዝ እንደ ሀገር መንግሥትነት ቀዳሚ ዕውቅና መስጠት ቢያስደንቅም

ጉዳዩ ያለቀለት ሻቢያ ኤርትራን ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠር እንደነበር የቅርብ ጊዜ የታሪክ መዝገብ ነው። ለዚህ ደግሞ በተጠያቂነት አብዛኛውን ድርሻ የሚወስደው የደርግ ፋሺስት አገዛዝ የጦረኝነት ፖሊሲ ነው ቢባል ሀቅን መቀበል ነው።

"የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው" "ባንዲራ ጨርቅ ነው" "አክሱም ለደቡቡ ምኑ ነው" "ነፍጠኞችን ከክልላችሁ አስወጡ" እያለ መርዙን ይዞ የመጣው ወያኔ ለባዕድና ለሻቢያ ያደረ፡ በኢትዮጵያዊነት ላይ የመንፈስ ቅናት የተጠናወተው፡ በሀገራችን ታሪክ በትረ ሥልጣን ይዞ ሀገርን እንደ መኾገር የሚበላና የሚያስበላ፡ የቤት ውስጥ ዓይጥ፡ የመንግሥት ወንበዴ ቢባል አግባብነት መኖሩ በተግባር እያደረገ ያለው ባህሪው ነውና ያስደንቅም።

ወያኔ ኢትዮጵያዊነት ላይ ያነጣጠረ አጀንዳውን በአንቀጽ 39 እውቅና አሰጥቶ ወቅት እየጠበቀ፡ ሀገር የመበታተን ቅድመ ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ለመሆኑ ሀገርን ለባዕዳን እየቸበቸበ፡ ሕጻናትን ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ ቋንቋቸውን፡ ባህላቸውን እንዲጠሉ እየኮተኮተና እየመረዘ፡ ወጣቶች ከሆዳቸው ይልቅ ሌላ እንዳያስቡ በረሃብ እየቀጣ፡ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያሉ ወገኖቻችንና የኦሮሞ ልጆችን በአሸባሪነት ስም በሽብር ጥይቱ እየፈጀ ሀገር ያማርሩ ዘንድ በዕቅድ የሚጓዝ የጥፋት መልዕክተኛ መሆኑ ከየትኞቹም አገዛዞች በላይ ልዩ ያደርገዋል።

ወያኔና ሻቢያ የዛሬ 20 ዓመት የነገሩንና የተመኙልን "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" ወያኔ እየሰጠን ይገኛል። ዛሬ ያልታየን፡ የነገ መዘዙ ከባድና ውስብስብ የሆነው፡ ለም መሬታችንን ለተለያዩ ባዕዳን ኃይሎች ችብቸባ በሰፊው ሊታይ ይገባዋል። የከተሞችን ቦታ በሊዝ ስም ለተለያዩ የውጭ ባለሀብቶች አሳልፎ መስጠቱ፡ ነገ መልሰን ለማግኘት ከባድ የሆነ አንዱ የቤት ሥራ መሆኑ ልናጤነው ይገባናል። የግብጽና የቱኒዝያ ሕዝባዊ ዐመጽ አስደንግጦት ጦርነት ቢያጣ ብሔራዊ ስሜት ይቀሰቅስልኛል ብሎ የጀመረው የእጻሴው ገንዘብ ዘረፋ ተግባራዊ ቢሆን እንኳ ካልጠፉ ሥነ ምድራዊ አካባቢ የዐባይን ግድብ ሱዳን ድንበር ላይ የማድረግ ዕቅዱ ከኛ ይልቅ በቀላሉ ማን ሊይዘውና ሊቆጣጠረው እንደሚችል ወደፊት የምናየው አንዱ የቤት ሥራ ክፍል መሆኑ፡ በምዕራብ ኢትዮጵያ ለሱዳን መንግሥት ልቅና ክፍት ከሆኑት መሬታችን ጋር ተያያዥነት ያለው ነገ ብጥብጥና ጦርነት ሊቀሰቅስ የሚችል በወያኔ የተቀበረ ፈንጂ የቤት ሥራችን አካል ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

በወያኔ የገጠር መሠረተ ልማት ፕሮግራም አበሳውን ያየውና እያየ ያለው አርሶ አደር ችግር፤ በማዳበሪያ አቅርቦት ሰበብ የመሬቱንና አፈሩን ተፈጥሮአዊ አብቃይነት መቆጣጠር፡ በቅይረ ብሄራይ ህይወታት (Genetically Modified) ፕሮግራም የተዳቀሉና የተበረዙ ሰብሎችን ከውጭ በማስገባትና ለዝርያ በማዋል የሀገራችንን ንጹህ ዝርያዎችን የማምከንና የማጥፋት ረቂቅ ተንኮል አንዱ የተሰጠን የቤት ሥራ ሆኗል።

ትውልድን ለማቀጨጭ ተወጥኖ የተዘጋጀው የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ሕፃናት ያለ ዕድሜያቸው የሀገር ሸክም፡ የቤተሰብ ተጧሪ እንዲሆኑና በጨቅላ አዕምሮአቸው የወደፊት ብሩህ ተስፋ እንዳይኖራቸው፡ ተስፋ ቆርጠው ሰለ ሀገራቸውና ሕዝባቸው ከማሰብ ይልቅ "የተሳካለት" ስለ ስደት ፡ ያልሆነለትም ስለ ሌብነትና ዘረፋ እንዲያስብ ከተዘጋጀለት ወጥመድ በተጨማሪ ወደፊትም ለሀገሪቱ በማንኛውም መስክ ብቁ ዜጋ፡ ሀገር ተረካቢ ትውልድ

እንዳይኖር የተሸረበው የወያኔ ሤራ  በሕብረተሰቡና በተተኪው ትውልድ ውስጥ ያስከተለው ወያኔ ሰራሽ ችግር ለመመለስ ከታቀደልን የመቶ ዓመት የቤት ሥራ አካል ነው።

አንዱን ዘር በሌላው፡ አንዱን ጐሳ ከሌላው፡ አንዱን ሃይማኖት ከሌላው ለማጋጨት፤ ለማተራመስ፤ ለማናከስ በተለያየ ጊዜ ለተወጠነው የወያኔ ከፋፋይ ፖሊሲ ላለመንበርከክና መሳሪያ ላለመሆን እርስ በርሱ እየተከባበረና እየተጠባበቀ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ  ከዚህ መርዘኛ የወያኔ ከፋፋይ አዙሪት ሳይሰነቀር አንድ ሕዝብ፡ አንድ ዜጋ፡ አንድ ኢትዮጵያዊ በመሆን ሌሎች ችግሮቹን እንደሚወጣ ጥርጣሬ ባይገባንም፡ የሰሞኑ የኦነግ የኢትዮጵያን አንድነት መቀበልና የኦሮሞ ብሔረሰብ ችግሮች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በጋራ ለመፍታት የተሰጠው መግለጫ በወያኔ "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" ውጥን ላይ ከፍተኛውን ዱላ ያሳረፈ ድጋፍ ሊቸረው የሚገባ አንድ እርምጃ ነው።

ከወያኔ ድብቅ ተልዕኮና ህልም አንዱ ሀገራችን ኢትዮጵያን መግዛትና እንደአሻው መቦጥቦጥ ጊዜው ሲያበቃለት፡ ትግራይን ይዞ ከሻቢያና ሱዳን ጋር በሚደረግ የጋራ ስምምነት ታላቋን ትግራይን እውን የማድረግ ቅዠቱ ነው። "እኔ ከሌለው ኢትዮጵያ አበቃላት" ፉከራውም በዘርና በሃይማኖት የቀበረው ፈንጂ እንደፍላጎቱ የሚቀጣጠልለት የሚመስለው የእብድና ደንባራ ዕቅዱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ለማንም ኢትዮጵያን ለመበታተን ለተነሱ ኃይሎች አሳልፎ ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይመለስ ሲያስጠነቅቀን ነበር። ለዚህም ከማንም ይበልጥ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለብን ባዮችን ለመጠቀም የነበረው ህልምና ምኞት በኦነግ የአቋም ለውጥ እንደተሰናከለበት ሁሉ ከዚህ ትምህርት በመውሰድ ኦብነግም በተመሳሳይ ትግሉን በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ያራምድ ዘንድ ይጠበቅበታል።

ኦነግ በ January 01, 2012 የወሰደው የአቋም ለውጥ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በተናጥል ደግሞ ለኦሮሞ ልጆች የዴሞክራሲ ትግል ጉልህ የሆነ እገዛ እንደሚያደርግ በመገንዘብ ተስፋ ሊኖረን ይገባል። የኦሮሞ ልጆች በተለያዩ ጨቋኝ፡ አፋኝና ዘረኛ አገዛዞች ተሰቃይተዋል፡ ታስረዋል፡ ተጨፍጭፈዋል፡ ተገድለዋል። ይህን ግፍና በደል አብረዋቸው የተጋሩና የመከራው ተቋዳሽ የሆኑ የአማራ፡ የትግራይ፡ የጉራጌ፡ የአፋር፡ የደቡብ፡ የሶማሊያ፡ ወዘተ. ልጆች መኖራቸውን ተገንዝበው ችግራቸው ኢትዮጵያ ሳትሆን "ከእጅ አይሻል ዶማ" አገዛዞች የፈጠሩት መሆኑን ተገንዝበው አንጋፋው ድርጅታቸው ኦነግ የአቋም ለውጥ ያደርግ ዘንድ ትልቁን አስተዋጽዎ ያደረጉት የኦሮሞ ልጆች ሊመሰገኑ ይገባል። ኢትዮጵያ ከማንም ባላነሰ የኦሮሞ ነች። በርካታ የኦሮሞ ልጆች ለኢትዮጵያ አንድነት ተሰውተዋል። በሚደረገው የዴሞክራሲና የመብት ትግል የኦሮሞ ልጆች ከሌላው ተበዳይ የኢትዮጵያ ልጆች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ዘምረዋል፡ ጮኸዋል፡ ግንባራቸውን በተደረገው የነጻነት ግብግብ ለፋሺስቶች ጥይት ሰጥተዋል። ይህን አኩሪ ታሪክ አሁንም ሊጠብቁና መብታቸውን ሊያስከብሩ የሚችሉትና የሚገባቸው ከሀገራቸው ሕዝብ ጋር መሆኑንና በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ሊሰለፉ ድምጻቸውን ሲያሰሙ ይህን የትግል ውጤት በአዎንታ መቀበል ተገቢና አግባብነት ያለው ነው።

ኦነግ በወሰደው የአቋም ለውጥ ድሉ የሁሉም ኢትዮጵያ ልጆች ነው። በብሔር/ብሔረሰብ የተደራጁ ድርጅቶች ቅድሚያ ለብሔር/ብሔረሰባቸው መብት መከበር ቢሰጡም፡ በሚደረገው የዴሞክራሲ ትግል ኦነግ ከፍተኛውን ድርሻ ይጫወት ዘንድ ካስፈለገ የተደረገው መሰረታዊ የአቋም ለውጥ አስፈላጊና እሰየው የሚያሰኝ ነው። በዚህ ሂደት የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ለጥያቄ የሚቀርብ አለመሆኑን ድምጻችሁን በማሰማት ሌት ተቀን የደከማችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች፡ የሲቪክ ማህበራት፡ ምሁራን፡ ታዋቂ ግለሰቦች፡ የሃይማኖት አባቶች፡ የፓል ቶክ ወገኖችና ሀገር ወዳድ ግለሰቦች ልትመሰገኑ ይገባል። የአንድነት ኃይሉ የኦነግን የመገንጠል ጥያቄ ይቀበል ዘንድ የወተወታችሁ፡ ያለማንም ተጽህኖ የኦነግ አመራር አካልና አባላት ከወሰዱት የአቋም ለውጥ ትልቅ ትምህርት ልትቀስሙ ይገባችኋል።

በትንሹ ለ40 ዓመት የተያዘን ከኢትዮጵያ የመገንጠል ጥያቄን ወቅቱ ያለፈበትና ከተጨባጩ የዓለምና የሀገራችን ሁኔታ አንጻር በመገምገም አዋጭ አለመሆኑን በመረዳት ኦነግ የወሰደው መሠረታዊ የአቋም ለውጥ በተለይ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች እራሳቸውን መመርመርና ድርቅናቸውን ትተው ማስተካከል የሚጠበቅባቸን አሠራር አስተካክለው ከመባላትና በውኃ ቀጠነ ከመነታረክ በመውጣት የትግሉን ሞተር ያሞቁት ዘንድ ዋናውን ትምህርት ሊወስዱ ይጠበቅባቸዋል።

ኦነግ ከወሰደው የአቋም ለውጥ ጋር በተያያዥነት ሊነሱና በቀጣይነት ሊተገብራቸው የሚገባ ጉዳዮች ይበልጥ ተአማኝነትን ለድርጅቱ በመስጠት የሚደረገውንም ፀረ-ወያኔ ተጋድሎ ከምንግዜውም የበለጠ አጠንክሮ ለመቀጠልና ለድልም ለመብቃት በር ከፋች ነውና አንዳንድ መታየት ያለባቸውን ጉዳዮች መጠቆም ግድ ይላል።

- ኦነግ በወሰደው የአቋም ለውጥ ተቃውሞአቸውን ያሰሙ ሌሎች የኦነግ ክፍሎችን በማወያየትና በማነጋገር ሙሉ በሙሉ ትግላቸውን በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ያደርጉ ዘንድ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።
- ኦነግ የወሰደው የአቋም ለውጥ ለኅብረት ምሥረታ ተብሎ የተደረገ ሳይሆን መሠረታዊ የሀገር ህልውና ጉዳይ መሆኑን በመቀበል፡ በቀጣይነት በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራት፡ ለመተባበርና ለመታገል መዘጋጀት አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ልዩነትን አቻችሎ በመግባባትና በመመካከር በመንዝ፡ የሚያጋጥሙ ማንኛውንም መሰናክልና ውጣ ውረድ በትዕግሥት ለማስተናገድና አካሄድን በአግባቡ በማሳመር ዋናው ትኩረት የወያኔን ሥርዓት በመጣልና በቀጣይነት አንድነቷን የጠበቀች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሥርዓት ግንባታ ላይ በማተኮር በጋራ ለመንዝ መዘጋጀት ያስፈልጋል።
- ኦነግ አሁን ከወሰደው የአቋም ለውጥ ጋር ተፃራሪነት ያላቸውን ክንውኖችና ድርጊቶች ያለምንም ማቅማማት መመርመር ይኖርበታል። ለምሳሌ፡ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት መቀበል፡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ መቀበልና ማክበር፡ ዘርን ያማከለ ክልላዊ አስተዳደርን ማስወገድ ወዘተ.

- በኢትዮጵያ አንድነት ከማያምኑት እንደ ኦብነግ ያሉ ድርጅቶች ጋር የተደረገው ስምምነትና አብሮ መጓዝ ከዚህ የኦነግ አቋም ጋር ተፃራሪነት አለውና እንደገና መታየት ያስፈልገዋል።

- ለኦነግም ሆነ ለማንኛውም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግላቸው ሀገር ተከል ይሆን ዘንድ የሚደረገው ጥረት መቀጠል ይኖርበታል። ለዚህም በሰላማዊ መንገድም ሆነ በትጥቅ ትግል የወያኔን አገዛዝ ለመጣል የሚታገሉ በመላ መከታቸውና መጠለያቸው የኢትዮጵያ ሕዝብና የቆሙለት ብሔር/ብሔረሰብ መሆኑን ተረድተው ከማንኛውም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ከሚጻረሩ ኃይሎችና አንድነቷን ከሚፈታተኑና መበታተኗን ከሚቋምጡ እንደ ሻቢያ ዓይነት ኃይሎች ጋር ያላቸውን ትስስርና ትብብር መስበር ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ኦነግ ጽ/ቤቱን ከአሥመራ ለማንሳትና ከሻቢያ ጋር ያለውንም ማንኛውንም ስምምነትና ትብብር ለማቋረጥ መዘጋጀት ይኖርበታል።

ከላይ በድጋሚ መመርመርና መታየት የሚገባቸው ጉዳዮች በቀጣይነት ግልጽ እየሆኑ መምጣት ይኖርባቸዋል። ኦነግ በወሰደው የአቋም ለውጥ ሰሞኑን እየተመለከተ ያለው ድጋፍ ማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ልጆችም የኢትዮጵያን አንድነት ፈላጊዎች መሆናቸውን መስካሪ ነው። ይህንን ድጋፍ ዘለቄታዊነት እንዲኖረውና ኦነግ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ተገቢውን ድርሻ ይወጣ ዘንድ ቀጣይ እርምጃዎችና አካሄዶች ተስፋ ሰጪ እንደሚሆኑ ይጠበቃል።

የኦነግንም ሆነ የኦብነግን የመገንጠል ጥያቄአቸውን ወደ ጎን አድርገው በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ያለውን ችግር በጋራ ለመፍታት ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ጋር በጋራ ለመምከር ከተነሱ ማንም የሚከፋ አይኖርም። የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት እንደገና መታደስ ለሀገር ዕድገትና ብልጽግና አስፈላጊነቱ አጠራጣሪ ባይሆንም በትንሹ ለ20 ዓመት በሀገራችን የተተከለ የዘር ድርጅትንና ዘረኝነትን በአንድ ጀምበር ማስወገድ እንደማይቻል አብዛኛው ሊስማማበት ይችላል። የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰችን ባህል፡ ቋንቋ፡ ቅርስ፡ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ሀብትነቱን በመገንዘብ በግልም በቡድንም ለመንከባከብ፡ ለመጠበቅ ለማዳበር የዘር ድርጅቶች ጠቀሜታነት ቢኖራቸውም፡ ኢትዮጵያዊነት ላይ ሲያነጣጥሩ ነው ችግሩ። የወያኔ ጠባብ የዘረኝነት ፖሊሲ በሌሎች ሳይደገም ሊያበቃ፡ ልንታገለው ይገባል። በአንጻሩም ይህ የዘር ፖለቲካ ለሀገራችን ያስከተለውን ቀውስ ከግምት በማስገባት፡ የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባትና ወያኔ የቀበረውን ብሔራዊ ስሜትን ለማደስ የሁሉንም ዜጋ ጥረት ይጠይቃል።

ዛሬ በመብት ስም፡ ሀገራችንን ለመበተን መነሳት የለብንም። በመብት ስም መገነጣጠልን ማራገብ አይኖርብንም። ኢትዮጵያ ሀገሬ ላለ ብሔር/ብሔረሰብ፡ አንዱ ለሌላው መብት መሟገት ያለበት ተያያዥነት ስላለው ነውና፡ የአንዱ ድል ከሌላው ሊነጠል አይችልምና፡ ለሀገርና ለሕዝብ መብት በጋራ መጮህ የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ የሚሆነው። ኦነግ የኦሮሞን ብሔር ኢትዮጵያዊነት ተቀብሎ ይዞ የተነሳው ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ

አካል መሆኑን እስከተቀበለ ድረስ፡ የኦሮሞ ሀገር መላዋ ኢትዮጵያ መሆኗን እስካመነ ድረስ የኦሮሞን ባህል፡ ቋንቋ፡ ቅርስ ለመጠበቅ በብሔር መደራጀቱ አስከፊነት አይኖረውም።

ወያኔና ሻቢያ እየሰጡን ያለው "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" አንዱ አካል ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በሀገርነት እንዳትኖር ማድረግ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ አፍሪካን እንደፈለጋቸው እየተቀራመቱና እየቦጠቦጡ ያሉ ባዕዳን ኃይሎች ጥቅማቸውን እንጂ ሕዝብን ተመልካች አይደሉምና የፈራረሰች ኢትዮጵያን፡ ጥንካሬዋን ያጣች አፍሪካን ይፈልጋሉ። ለዚህ ደግሞ እንደ ወያኔ ያለ የታሪክ እንግዴ ልጅ ተመችቷቸዋል። ኢትዮጵያን ለውስብስብ መከራ እያዘጋጀ ያለው ወያኔ "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" መሰሪ ተንኮል አየር ላይ እንዲቀር ያደረገው የኦነግ አቋም ለትግራይ ተወላጆች ትልቅ ትምህርት ሊሰጥ ይገባዋል። የኦሮሞ ልጆች ትግላችን በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ብለው እንደተነሱ ሁሉ የትግራይ ልጆችም በስማችን መነገዱ ያብቃ የማለት ታሪካዊ ኃላፊነት አለባችሁና የወያኔን "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" ዕርቃኑን አስቀሩት።

ኢትዮጵያ ሀገራችን የሰው ልጆች የዜግነት መብት የተከበረባት፡ አዛውንት እናትና አባቶች እይታ የሚያገኙበት፡ ሕጻናት በእንክብካቤና በጤና የሚያድጉባት፡ ወጣቶች ሀገር ተረካቢ ብቁ ዜጋ ይሆኑ ዘንድ የሚመቻችበት፡ በመላው ዓለም በስደት የሚንገላቱ ወገኖች ሀገራቸውን የሚያዩበት፡ የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ባህል፡ ቋንቋ የሚጠበቅበትንና ታሪካዊ የሀገራችን ቅርሶችና የተፈጥሮ ሀብቷ ጥበቃና እንክብካቤ አግኝቶ ኢትዮጵያችን የልጆቿ የምትሆንበትን የድል ቀን ለማብሰር በአንድነት እንነሳ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

አሉላ (alulla2@yahoo.com)

ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ.ም. (January 05, 2012)